የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የዳኞች ዝውውርና ምደባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር

2/2007 ዓ.ም

ባህር ዳር

ግንቦት 2007 ዓ.ም

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች/የተሿሚዎች የዝውውር እና የምደባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/2007 ዓ.ም

መግቢያ

በክልሉ ውስጥ በአሉ ፍርድ ቤቶች ተመድበው የሚሰሩ ዳኞች እና ሌሎች የጉባኤ ተሿሚዎች የሚያቀርቡትን የዝውውር እና የምደባ ጥያቄ ግልፅነት እና ተጠያቂነት በሰፈነበት መንገድ መፈፀም በማስፈለጉ፣

ዳኞች እና የጉባኤ ተሿሚዎች የሚያቀርቡትን የዝውውር እና የምደባ ጥያቄ በግልፅ በታወቀ እና ተገማች በሆነ መስፈርት መመለስ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት፣

የሚቀርቡ የዝውውር እና የምደባ ጥያቄዎች ፍታዊነትን፣ የስራ ፍሰትን እና ለህዝብ አገልገሎት መሰጠትን ግምት ውስጥ በአስገባ መንገድ መመለስ ተገቢ በመሆኑ፣

በአስቸጋሪ ቦታዎች ተሹመው የሚሰሩ ዳኞች እና ሌሎች የጉባኤ ተሿሚዎች ለአበረከቱት አስተዋፅኦ ተገቢውን ክብር መስጠት እና በዝውውር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም ከዞን ዞን ያለውን ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ዝውውር እና ምደባ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 /ለ/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን ይህንን የዝውውርና የምደባ መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሄራዊ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች/ተሿሚዎች

የዝውውር እና የምደባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2007 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "ጉባኤ ወይም ንዑስ ጉባኤ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በአዋጅ ቁጥር 209/2006 ዓ.ም የተቋቋመውን የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ወይም የዞን ንኡስ ጉባኤ ነው፣

2. "ዳኛ " ማለት በአዋጅ ቁጥር 223/2007 በአንቀጽ 2/ሠ/ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፣

3. "የስራ ሂደት" ማለት በፍርድ ቤቶቸ ውስጥ ውጤት ለማምጣት የዳኛ ወይም የችሎት ስራ አፈፃፀም ደረጃ በደረጃ የሚያከናውናቸው ተያያዥነት እና ተከታታይነት ያላቸው ተግባራት ከመነሻ እስከ መድረሻ የሚከናወንበትን የስራ ፍሰት የሚያሳይ አደረጃጀት ነው፣

4. "የወረዳ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ" ማለት ከአሉት ዳኞች መካከል የወረዳ ፍርድ ቤቱን ስራ በሀላፊነት እንዲመራ እና እንዲያስተባብር በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተሹሞ የሚሰራ ዳኛ ነው፣

5. "የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ" ማለት ከአሉት ዳኞች መካከል የችሎቱን ስራ በሀላፊነት እንዲመራ እና እንዲያስተባብር በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አማካኝነት ተሹሞ በችሎት ሰብሳቢነት የሚሰራ ዳኛ ነው፣

6. "የስራ ሂደት አስተባባሪ" ማለት በየደረጃው በአሉ ፍርድ ቤቶች የአንድን የስራ ሂደት /ክፍል ስራ ከመነሻ እስከ መድረሻ ድረስ እንዲከናወን የማቀድ፣ የመፈፀም፣ አፈጻጸምን የመከታተል፣ የማልማት፣ የመገምገም፣ የመመዘንና የማበረታታት ተግባሮችን እንዲያከናውን በጉባኤ ሀላፊነት የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ነው ፣

7. "የጉባኤ ተሿሚ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 209/2006 ዓ.ም መሰረት በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ወይም በዞን ንኡስ ጉባኤ በሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኝነት፣ በቃዲ ዳኝነት፣ በሬጅስትራርነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት፣ በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ወይም ንኡስ ጉባኤ ጽ/ቤት ሀላፊነት ወይም በዳኛ ደረጃ የስራ ሂደት መሪ ወይም ባለሙያ ሆኖ እንዲሰራ የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ነው፣

8. "ዝውውር" ማለት ተሿሚው በራሱ ፈቃድ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ተሿሚው ቀድሞ የሚያገኘውን ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንደያዘ ከነበረበት የሥራ ቦታ ወይም መደብ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም መደብ አዛውሮ መሥራት ነው፣

9. “ምደባ” ማለት ከሕግ ት/ቤት ወይም ከሕግ ማሰልጠኛ ተቋም የመጡ ዳኞች፣ ረዳት ዳኞች እና የጉባኤ ተሿሚዎች በሚመጥናቸው የሥራ መደብ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት መድቦ ማሰራት ነው፣

10. “አገልግሎት” ማለት በፍርድ ቤቶች ወይም በሌላ መ/ቤት የተሰጠ የስራ አገልግሎት ነው፣

11. “የስራ ልምድ” ማለት ህጋዊ እወቅና ካለው የመንግስት፣ የግል፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ወስጥ በየወሩ ቋሚ ደመወዝ እየተከፈለው ስራውን ለሚያሰራው መ/ቤት በመደበኛ የስራ ሰዓት የተወሰነ ስራ በማከናወን የተገኘ የስራ ልምድ (ችሎታ) ነው፣

12. “አግባብ ያለው ወይም ቀጥተኛ የሆነ የስራ ልምድ” ማለት ለአንድ የዳኛ/የተሿሚ ደረጃ በሚፈፀም ስምሪት ላይ ከስራ ደረጃው ተግባር እና ሀላፊነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የስራ ልምድ (ችሎታ) ነው፣

13. “አግባብነት የሌለው ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የሥራ ልምድ” ማለት በዳኝነትና በሕግ ሙያ ከተሰጠ አገልግሎት ውጭ ያለ የሥራ ልምድ ነው፣

14. “ምድብ ቦታ” ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤቶች እና የወረዳ ፍ/ቤቶች እንደአየር ፀባያቸው እና የኑሮ ምቹነታቻው ታይተው በሶስት ምድብ የሚደለደሉበት ነው።

3. የመመሪያ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ በከፍተኛ ፍ/ቤት ኘሬዚዳንቶች፣ በከፍ/ፍ/ቤት ዳኞች፣ በወረዳ ፍ/ቤት ዳኞች፣ በሰብሳቢ ዳኞች፣ አዲስ በሚመደቡ ዳኞች፣ በሪጅስትራሮች፣ በተከላካይ ጠበቆች፣ በሸሪያ ዳኞች እና በሌሎች የጉባኤ ተሿሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. የመመሪያው ዓላማ

1. የተሿሚዎች ዝውውር እና ምደባ በግልፅ በታወቀ መስፈርት፣ ወጥነት በአለው እና ተጠያቂነት በሚያመጣ አግባብ እንዲከናወን ለማድረግ፣

2. በየደረጃው የሚገኙ ተሿሚዎች በተመደቡበት ቦታ ተረጋግተው የዳኝነት ሥራቸውን ማከናወን እንዲችሉ ለማድረግ፣

3. ተሿሚዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረው መሥራት መብታቸው ቢሆንም ዝውውሩ የሥራን ፍሰትን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ እንዲቻል፣

4. ተሚሿዎች በሚሰጡት የዳኝነት ሥራና አገልግሎት አሰጣጥ እምነትና እርካታ እንዲኖር ለማስቻል፣

5. በሕግ ሙያ ተመርቀው እና ሥልጠና ወስደው የወጡ ዳኞችን አስፈላጊ የሰው ኃይል በጠየቀበት ቦታ በመደልደል ማሰማራት እንዲቻል ለማድረግ ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ ዝውውር እና ምደባ አፈፃፀም

5. ዝውውር የሚፈፅሙ አካላት

1. የክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ከዞን ወደ ዞን የሚደረግ ዝውውር እና ምደባን ይፈፅማል፣
2. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ በአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀፅ 14/5/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የስራ ፍሰቱ የሚጠይቅ ሲሆን እና በጤና ችግር ምክንያት ዳኞችን አዛውሮ ማሰራት ይችላል። እንዲህ በሆነ ጊዜ የተፈፀመውን ዝውውር ለጉባኤው ያሳውቃል፣
3. የዞን የዳኞች አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ በዞኑ ውስጥ ከአለ አንድ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ዝውውር እና ምደባ ይፈጽማል።

6. ዝውውሩ የሚፈፀምባቸው ደረጃዎች

1. ከአንደ ዞን ወደ ሌላ ዞን
2. ከአንድ ዞን ወረዳ ወደ ሌላ ዞን ወረዳ

7. ዝውውርና ምደባ ከመፈፀሙ በፊት መከናወን ያለባችው ተግባራት

1. የመዝገብ ክምችትና የስራ ፍሰቱ የበዛ ሆኖ ተጨማሪ የሰው ኃይል የሚያስፈልግ መሆኑ ማረጋገጥ አለበት፣
2. ዝውውር መጠየቂያ ፎርም ለሁሉም የከፍ/ፍ/ቤቶች እና የወረዳ ፍ/ቤቶች እንዲደርስ ይደረጋል፣
3. የዝውውር ፎርሙ በዝውውር ጠያቂዎች ተሞልቶ፣ ተፈርሞበት እና ቅጹ በጥንቃቄ ተሞልቶ በየደረጃው ለሚገኙ አካላት መድረስ ይኖርበታል፣
4. ለዳኝነት የሚደርግ ዝውውር እና ምደባ አስቀድም የተፈቀደ ክፍት ደረጃ እና በጀት መኖሩ መረጋገጥ አለበት፣

8. ዝውውር ወይም ምደባ የሚፈፀምባቸው መስፈርቶች

1. መደበኛ በሆነ ዝውውር ተወዳድሮ የሚፈልጉትን ቦታ ለማግኘት የሚቻለው በሚከተሉት መስፈረቶች መሰረት በውድድር ይሆናል።

    ሀ. አገልግሎት(የስራ ልምድ)

    ለ. የስራ አፈፃፀም

    ሐ. የማህደር ጥራት

    መ. ፆታ

    ሠ. ጋብቻ

2. መደበኛ ባልሆነ ዝውውር ለመዛወር የሚቻለው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክያቶች ውስጥ አንዱ ሲያጋጥም ነው።

    ሀ. የጤና ችግር

    ለ. በስራ ምክንያት

9. መስፈርቶቹ የሚይዙት ነጥብ

9.1 መደበኛ የሆነ ዝውውር

ከዚህ በታች ከፊደል ተራ ቁጥር ከሀ-ሠ የተዘረዘሩትን መስፈረቶች መሰረት በማድረግ ለአንድ ቦታ ከአንድ በላይ ተወዳዳሪ ሲኖር ተወዳዳሪው በመስፈርቶቹ የአገኘው ጠቅላላ ውጤት ተደምሮ አብላጫ ውጤት ያገኘው የጠየቀውን ቦታ በዝውውር እንዲያገኝ ይደረጋል።

ሀ) አገልግሎት (የስራ ልምድ) ከ 50% ይይዛል

1) አገልገሎት(የስራ ልምድ) ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ከሆነ ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሰውን ውጤት ያገኛል፦

ሀ. ከ 2 እስከ 5 አመት ከ 11 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው----------15%

ለ. ከ 6 እስከ 9 አመት ከ 11 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው----------20%

ሐ. ከ 10 እስከ 13 አመት ከ 11 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው----------25%

መ. ከ 14 እስከ 17 ዓመት ከ 11 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው------30%

ሠ. ከ 18 እስከ 21 ዓመት ከ 11 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው-------35%

ረ. ከ 22 እስከ 25 ዓመት ከ 11 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው------40%

ሰ. ከ 25 አመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ላለው---------- 50%

ነጥብ ያገኛል፣

2) ከ 2 አመት በታች አገልግሎት ያላቸው አዲስ ዳኞች በልዩ ሁኔታ ከአልሆነ በስተቀር በመደበኛ ዝውውር ማዘወር አይቻልም፣

3) አገልግሎት ወይም የስራ ልምዱ ቀጥተኛ ካልሆነ ልምዱ በ 0.25 እየተባዛ ከላይ የተገለፀው ነጥብ እንዲሰጥው ይደረጋል።

ለ) የስራ አፈፃፀም ከ 32% ይይዛል

1) የተገኘው የስራ አፈፃፀም በ 0.32 እየተባዛ ይያዛል፣

2) ለዝውውር ለመወዳደር ቢያንስ የሁለት ጊዜ የስራ አፈፃፀም ሊኖር ይገባል፣

3) በዚህ አንቀፅ በተራ ቁጥር ለ(2) ላይ የተገለፀው ቢኖርም ዝውውሩ የሚካሄድበት ፍርድ ቤት ተጨባጭ ምክንያት ካለው እንደ ሁኔታው የአንድ ጊዜ የስራ አፈፃፀም ብቻ ወይም እንደ ነገሩ ሁኔታ በሌሎች መስፈርቶች ብቻ ላይ ተመስረቶ ዝውውር ሊሰራ ይችላል።

ሐ) የማህደር ጥራት ከ 5% ይያዛል

1) ከባድ የዲስፒሊን ቅጣት የተወሰነባቸው ዳኞች/ተሿሚዎች ቅጣቱን እስኪፈፅሙ ድረስ ለዝውውር መቅረብ አይችሉም። ቅጣቱን ከጨረሱ በኋላ ግን የቅጣቱ ውሳኔ ከአረፈበት ቀን ጀምሮ በተሻሻለው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች የዲሲፒሊን እና የስነምግባር ደንብ ቁጥር 14/2007 በአንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ 3(ሐ እና መ) በተደነገገው መሰረት የቅጣት ማቆያ የጊዜ ገደብ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ላይ የተመለከተው ነጥብ እየተቀነሰባቸው እንዲወዳደሩ ይደረጋል፣

ተ.ቁ	የተወሰደው የዲስፒሊን እርምጃ	የሚቀነስ ነጥብ	የሚሰጥ ነጥብ
1	ከደረጃ እና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ	5	0
2	እስከ አራት ወር ሊደርስ የሚችል የደመወዝ ቅጣት	4	1
3	እስከ አንድ ወር ደመወዝ የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት	3	2
4	የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ቅጣት	2	3
5	የቃል ማሰጠንቀቂያ ቅጣት(በፅሁፍ የተሰጠ ከሆነ)	1	4
6	ምንም የቅጣት ሪከርድ የሌለበት	0	5

2) የተወሰነባቸው የቅጣት መጠን ቀላል የዲስፒሊን ቅጣት ከሆነ ተሿሚዎች በማንኛውም ጊዜ ከዝውውር አይታገዱም፣

መ) ለፆታ እና ለአካል ጉዳት የሚሰጥ ነጥብ

1) ዝውውር ጠያቂዋ ሴት ከሆነች 3% ለፆታ የሚሰጥ ነጥብ ተጨማሪ ተይዞላት እንድትወዳደር ይደረጋል፣

2) በዝውውር ወቅት አንድ ሴት እና አንድ ወንድ ተወዳድረው እኩል ቢመጡ ቅድሚያ ለሴቷ ይሰጣል፣

3) በዝውውር ወቅት የአካል ጉዳተኞች ካሉ ከሌሎች ጋር ተወዳድረው እኩል ከአመጡ ቅድሚያ ለአካል ጉዳተኞች ይሰጣል።

ሠ) ለጋብቻ የሚሰጥ ነጥብ **10%**

ከዚህ በታች ያሉትን የጋብቻ መስፈርቶች የሚያሟላ የዝውውር ጥያቄ በውድድር ወቅት 10% ነጥብ ይያዝለታል

1) ጋብቻ ያላቸው ዳኞች ዝውውር ወይም ምደባ ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት ጋብቻ የመሠረቱ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅቸዋል፣

2) በጋብቻ ምክንያት ዝውውር ለመጠየቅ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ህጋዊ ከሆነ ተቋም ማቅረብ እና ማህደራቸው ጋር ተያይዞ መገኘት ይኖርበታል፣

3) በጋብቻ ምክንያት ለመዛወር ከሁለቱ ተጋቢዎች መካከል አንዱ ዳኛ ወይም የጉባኤ ተሿሚ ወይም ሌላኛው ተጋቢ የሌላ መ/ቤት ባልደረባ ወይም በግል የሚሰራ ሊሆን ይችላል፣

4) ሁለቱም ተጋቢዎች ዳኞች ወይም የጉባኤ ተሿሚዎች ከሆኑ ከፍ ያለ አገልግሎት ወደ አለው ሌላኛው ተጋቢ ዝውውር መጠየቅ ይቻላል። ዝውውር የተጠየቀው አካልም የስራ ፍሰቱን፣ የተጋቢዎችን የስራ ሁኔታ እና ሌሎችንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ አስገብቶ ተጋቢዎቹ ወደ አሉበት ወይም ተቀራራቢ ወደ ሆነ ቦታ በልዩ ሁኔታ ሊያዛውር ይችላል፣

5) ባልና ሚስት ዳኞች ወይም የጉባኤ ተሿሚዎች ከሆኑ ወይም ከሁለት አንዱ የሌላ መ/ቤት ባልደረባ ከሆነ የሚሰጠው 10% ነጥብ ተጨምሮ ዝውውሩ የሚፈፀም ሲሆን ከተወዳዳሪዎች ጋር እኩል ነጥብ ከአመጡ ቅድሚያ ለባለትዳሮች ይሰጣል።

9.2 ከዚህ በላይ በአንቀፅ 9 በንኡስ አንቀፅ 1 ከሀ እስከ ሠ የተዘረዘሩት ቢኖሩም በዝውውር ለተጠየቀው ቦታ ተወዳዳሪ የማይኖር ወይም ሁሉንም ዝውውር የጠየቁትን ተሿሚዎች ለመመደብ የሚያስችል ክፍት ቦታ እና የስራ ፍሰት ካለ ነጥቡ ተደምሮ ተወዳዳሪዎቹ ሁሉም እንዲዛወሩ ይደረጋል።

9.3 *መደበኛ ያልሆነ ዝውውር*

ከዚህ በተቻ በተራ ቁጥር 1 ና 2 የተጠቀሱት ምክንያቶች ሲያግጥሙ ዝውውርን በማንኛውም ጊዜ ማድረግ ይቻላል።

1. በጤና ምክንያት የሚደረግ ዝውውር

በጤና ምክንያት ዝውውር የሚጠይቅ ተሿሚ ህጋዊ ከሆነ ተቋም በሶስት ሀኪሞች/ዶክተሮች የህክምና ቦርድ አባላት የተፈረመ የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ዝውውሩ የቀረበለት አካልም በአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀፅ 14/5/ መሰረት ዝውውሩን ያለውድድር ሊፈቅድ እና ለጉባኤው ሊያስውቅ ይችላል፣

2. በሥራ ምክንያት በሚፈጠር ችግር የሚደረግ ዝውውር

1) የተሿሚው ቤተሰብ በፈጠሩት ችግር ምክንያት (ለምሳሌ በሌላ ሰው ላይ ግድያ ቢፈፅሙ) ወይም በሌላ ተጨባጭ ምክንያት በተሿሚው ላይ አደጋ ሊፈጥር የሚችል መሆኑ ሲታመን ወይም

2) ተሿሚው በሥራው አጋጣሚ ምክንያት በቦታው ቢቀጥል በእሱ ላይ ወይም በቤተሰቡ ላይ ችግር የሚፈጠርበት መሆኑ ሲታመን በተመሣሣይ ቦታና መደብ በአዋጅ ቁጥር 209/2006 አንቀፅ 14/5/ መሰረት ዝውውሩን ያለውድድር ሊፈቅድ እና ለጉባኤው ሊያስውቅ ይችላል፣

10. አዲስ የሚሾሙ እና ከትምህርት የሚመለሱ ዳኞች የምደባ አፈፃፀም

1. አዲስ የሚሾሙ ዳኞች ምደባ የሚካሄደው ከዚህ በፊት የነበሩ ዳኞች ዝውውር ከተሰራ በኋላ ክፍት በሚሆን ቦታ ላይ ይሆናል፣
2. አዲስ የሚመደቡ ዳኞች በአለው ክፍት ቦታ ላይ ተመስረቶ ምደባቸው በእጣ ይከናወናል፣
3. የእጣው ስነስርዓት በግልፅ በታወቀ ቦታ እና ሰዓት ተመዳቢዎቹ /ተወካዮቻቸው/ በሚገኙበት ሁኔታ በግልጽ ይከናወናል።
4. የእጣ ስነስርዓቱ እንደተከናወነ እና የምድብ ቦታቸውን እንዳወቁ እርስ በርስ ለመዘዋወር ቢፈልጉ በአንድ ቀን ውስጥ በፀሁፍ ስምምነታቸውን ምደባ ለሚያካሄደው አካል ማቅረብ ይችላሉ። ምደባ የሚሰራው አካልም ሌላ ተጨባጭ ምክንያት ከሌለው በስተቀር ስምምነታቸውን ተቀብሎ ምደባውን ሊያስተካክል ይችላል፣

5. በአዲስ የሚሾሙ ዳኞች ባለትዳር ሆነው የጋብቻ ማስረጃ የሚያቀርቡ ከሆነ ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ በተቻለ መጠን በአንድ ቦታ ላይ ምደባ ሊደረግላቸው ይችላል፣
6. ለሥልጠና ወይም ለትምህርት የተላከ ዳኛ ሥልጠናውን ወይም ትምህርቱን ጨርሶ ሲመለስ በነበረበት ቦታ ተመድቦ እንዲሰራ ይደረጋል።

ክፍል ሶስት

ስለ የቦታ ደረጃ እና ዝውውር የሚፈፀምበት ጊዜ

11. የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤቶችና ወረዳ ፍ/ቤቶችን በደረጃ ምድብ ቦታ ስለመደልደል

1. ዞኖች በመልከአ ምድር አቀማመጣቸው፣ በአየር ፀባያቸው፣ በመሠረተ ልማት ደረጃቸው እና የኑሮ ምቹነታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በሶስት ደረጃ ተከፍለዋል።

ሀ) ደረጃ አንድ ምድብ ቦታ

1) ባሕር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
2) ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት
3) ሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ለ) ደረጃ ሁለት ምድብ ቦታ

1) ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
2) ምሥራቅ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
3) ምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
4) ሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
5) ደቡብ ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
6) ኦሮሚያ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
7) አዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ሐ) ሶስተኛ ደረጃ ምድብ ቦታ

ዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት

2. የዞን የዳኞች አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ የወረዳ ፍ/ቤቶችን ከላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሰረት በማድረግ በሶስት ደረጃ ከፍሎ የቦታ ምደባ ያደርጋል።

3. ከአንድ ዞን ወረዳ ወደ ሌላ ዞን ወረዳ ዝውውር የጠየቀ ዳኛ ወይም የጉባኤ ተሿሚ ሲኖር ከዚህ በፊት በዳኝነት ወይም በጉባኤ ተሿሚነት የሰራባቸውን ወረዳዎች እና የወረዳዎቹን የቦታ ምድብ በዝውውር መጠያቂያ ፎረሙ ላይ አብሮ ሞልቶ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መላክ ይኖርበታል።

4. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከዞን ዞን የተጠየቀውን ዝውውር ከፈቀደ የሰራባቸውን ወረዳዎች እና የቦታዎቹን ደረጃ አያይዞ ለሚቀበለው ዞን መላክ ይኖርበታል፣

5. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሁን የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዝውውር በሚሰራበት ጊዜ በአንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ምድብ ቦታ ላይ ለሰራ ዳኛ/ ተሿሚ አገልግሎቱን በ 1.5 እያባዛ እንዲዝለት የሚደረግ ሲሆን በአንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 1 /ሐ/ ምድብ ቦታ ላይ የሰራ ዳኛ/ተሿሚ ከሆነ ደግሞ አገልግሎቱ በ 2 እየተባዛ እንዲያዝለት ይደረጋል፣

6. ማንኛውም ዳኛ ወይም ተሿሚ የተለየ ምክንያት ከሌለው በስተቀር በተመደበበት ዞንም ሆነ ወረዳ ሁለት ዓመት የማገልገል ግዴታ አለበት። ነገር ግን ሁለት አመት ሳይሞላው አዲስ ዳኞች ከተመደቡ ተሿሚው ዝውውር የጠየቀ ከሆነ ዝውውሩ በልዩ ሁኔታ ሊታይለት ይችላል።

7. ከላይ በአንቀፅ 9 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቶ ከአንደ ዞን ወደ ሌላ ዞን የተዛወረ ዳኛ ወይም ተሿሚ በዞኑ ውስጥ የሚመደበው ከሌሎች የዞኑ ተወዳዳሪዎች ጋር እኩል ተወዳድሮ የሚመደብ ሲሆን፤ በነበረበት ዞን ወይም ወረዳ በምድብ ሁለት እና ሶስት ላይ የሰራ ከሆነ አገልግሎቱ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ በተደነገገው መሠረት ታስቦ በአገኘው ውጤት መሰረት የሚመደብ ይሆናል።

8. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 7 የተገለፀው ቢኖርም ዞኑ ዝውውር ሰርቶ ምደባ ከጨረሰ በኋላ የተዛወረ ተሿሚ ከሆነ ዞኑ ከዳኛው ጋር በመመካከር አገልግሎቱ እና ሌሎች መስፈርቶች ታይተው በሚመጥነው ቦታ ላይ ሊመደብ ይችላል። የዚህ አይነት ችግር በዘላቂነት እንዳያጋጥም ግን ዞኖች ከወረዳ ወደ ወረዳ የሚያደርጉትን ዝውውር የሚሰሩት ክልሉ ከዞን ዞን የሚያደርገው ዝውውር ከተጠናቀቀ በኋላ ወይም ክልሉ ዝውውር እንደማያደርግ ከአሳወቃቸው በኋላ ይሆናል፣

9. ዳኛው/ተሿሚው ዝውውር ሲደረግለት ቀድሞ ይዞት የነበረውን ጥቅማ ጥቅም እና ደረጃ እንደያዘ ይሆናል።

12. ዝውውር እና ምደባ የሚፈፀምበት ጊዜ

1. በክልል እና በዞን ደረጃ የሚደረግ መደበኛ ዝውውር በአመት አንድ ጊዜ የሚከናወን ይሆናል። በዚህ መሰረት ከዞን ዞን የሚደረግ መደበኛ ዝውውር በሀምሌ ወር መጨረሻ ዳኞች እረፍት ከመውጣታቸው በፊት ይከናወናል፣

2. ከወረዳ ወደ ወረዳ የሚደረግ መደበኛ ዝውውር በሁለት መልክ የሚካሄድ ይሆናል።

    1) አዲስ ዳኞች ሲሾሙ ወይም ስልጠናቸውን ጨርሰው ወደየዞኑ በሚመደቡበት ጊዜ፣

    2) አዲስ የሚመደቡ ዳኞች ከሌሉ በአመት አንድ ጊዜ በነሀሴ ወር መጀመሪያ ይካሄዳል፣

3. በክልል ደረጃ በአመት አንድ ጊዜ ለሚካሄደው ዝውውር ዞኖች የዝውውር ፎረሙን ሞልተው እስከ ሰኔ 30 ድረስ ለክልል ማድረስ አለባቸው። ለዚህ ዓላማ ሲባል ተሿሚዎች የዝውውር ፎርም እንዲሞሉ የሚደረግበት ጊዜ እስከ ግንቦት 30 ድረስ ብቻ ይሆናል፣

4. ከዞን ዞን እና ወረዳ ወረዳ ለሚደረግ ዝውውር የዝውውር ጠያቂዎች ከአንድ እስከ ሶስት ቦታዎችን በደረጃ መሙላት ይኖርባቸዋል። በዚህ ጊዜ ጥንቃቄ ማደረግ ያለባቸው የሞሏቸውን ቦታዎች በመስፈረቱ መሰረት ተወዳድረው እንዲያገኙ ከተደረገ እና ከተወሰነ በኋላ እንደገና ማሻሻል የማይችሉ መሆኑን ነው፣

5. ዝውውር የተፈፀመለት ዳኛ/ተሿሚ ወደ ተዛወረበት ቦታ ክሊራንስ በመያዝ ከ 10 የስራ ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ያላደረገ ዳኛ/ተሿሚ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከአላጋጠመው በስተቀር ስራውን በገዛ ፈቃዱ እንደለቀቀ ተቆጥሮ ይሰናበታል። ነገር ግን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው ዳኛ/ተሿሚ ከአቅም በላይ የሆነው ችግር እንደተወገደ በ 5 የስራ ቀን ውስጥ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል። የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ከሆነ ስራውን እንዲቀጥል ይደረጋል። በምድብ ቦታው ባለመገኘቱ ምክንያት በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ ከሆነ ይኸው እንዲታወቅ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፣

6. በስራ አስፈላጊነት፣ በጤና እና በጋብቻ ምክንያት የሚደረግ ዝውውር መደበኛ የዝውውር ጊዜን ሳይጠብቅ በማናቸውም ጊዜ ክፍት ደረጃ እና በጀት ያለ መሆኑ እየተረጋገጠ ከመደበኛ የውድድር ጊዜ ውጭ ሊደረግ ይችላል፣

7. በስራ ምክንያት ወይም አዲስ ዳኞች በአለመመደባቸው ምክንያት መደበኛ ዝውውር ለማድረግ ከአልተቻለ ዝውውር እስኪደረግ ድረስ በጊዜያዊነት አዛውሮ ማሰራት ይቻላል።

13. የስራ ሂደት አስተባባሪ እና የሰብሳቢ ዳኛ ዝውውርን በተመለከተ

1. የስራ ሂደት አስተባባሪ ወይም የሰብሳቢ ዳኛ ዝውውር የሚደረገው ተመሳሳይ የሆነ ቦታ እና በጀት ሲኖር ይሆናል፣

2. በዚህ መሰረት የሂደት መሪ/አስተባባሪ ወይም ለሰብሳቢ ዳኛ ክፍት በሆኑ ቦታዎች ማስታወቂያ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸውን ተሿሚዎች በዝውውር መስፈርቱ መሰረት አወዳድሮ ማዛወር ይቻላል፣

3. በዝውውር የሚሄድ የሂደት መሪ/አስተባባሪ ወይም ሰብሳቢ ዳኛ ከጠፋ ግን የደረጃ እድገት መስፈርትና ማስታወቂያ ወጥቶ ሰብሳቢ ዳኛ ወይም የስራ ሂደት መሪ/ አስተባባሪ እንዲመደብ ይደረጋል፣

4. ከሂደት ሂደት የደረጃ እና የጥቅም ልዩነት ሳይኖር የሚደረግ የዳኛ ዝውውር የስራ ፍሰት እየታየ በሰብሰቢ ዳኛ ወይም ፕሬዚዳንት አማካኝነት ብቻ ሊፈፀም ይችላል።

ክፍል አራት

የዝውውር ፈፃሚ አካሎች ተግባር እና ኃላፊነት

14. የጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተግባር እና ኃላፊነት

1. የዝውውር መጠየቂያ ፎርሞችን ለዞኖች ወቅቱን ጠብቆ ማሰራጨት እና መቀበል፣

2. ተወዳዳሪዎች ለጠየቁት የዝውውር ቦታ በመስፈርቱ መሠረት አወዳድሮ በጉባኤው ያስወስናል። ይኸው እንዲታወቅ በግልጽ በሰሌዳ ላይ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

3. በዝውውሩ ወይም በተደረገው ምደባ ቅሬታ ካለ ቅሬታውን ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፣

4. የዝውውር ወይም የምደባውን ደብዳቤ ሰጥቶ ወደ ተመደቡበት ቦታ ያሰማራል፣

5. ሌሎች ከዝውውርና ከምደባ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

15. የዞን ከፍ/ፍ/ቤት ንዑስ ጉባዔ ተግባር እና ኃላፊነት

1. በዞኑና በወረዳ ያለውን የመዝገብ ክምችትና የስራ ፍሰት በመለየት የሚፈለገውን የሰው ኃይል መጠየቅ፣

2. የዝውውር ፎርሙ ለዞኑ ዳኞች እና ለየወረዳዎቹ ወቅቱን ጠብቆ ማሰራጨት፣ ትክክለኛነቱን አረጋግጦ እና ሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቆ ማድረስ፣

3. በዝውውር ወይም በምደባ የተላኩትን ተሿሚዎች ደብዳቤና ክሊራንስ መያዛቸውን አረጋግጦ መድቦ ማሰራት ፣

4. ወደ ሌላ ዞን የሚዛወሩትን ተሿሚዎች በወቅቱ ክሊራንስ መስጠትና ወደ ሚሄድበት ቦታ መላክ ይኖርበታል፣

5. ከምደባና ዝውውር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

16. የወረዳ ፍርድ ቤቶች ኃላፊነት

1. በወረዳ ውስጥ ያለውን የመዝገብ ክምችትና የስራ ፍሰት በመለየት የሚፈለገውን የሰው ኃይል መጠየቅ፣
2. የዝውውር ፎርሙ በወረዳው ውስጥ ላሉት ዳኞች ወቅቱን ጠብቆ ማሰራጨት፣ ትክክለኛነቱን አረጋግጦ እና ሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቆ ማድረስ፣
3. በዝውውር ወይም በምደባ የተላከለትን ተሿሚ ደብዳቤና ክሊራንስ መያዙን አረጋግጦ መድቦ ማሰራት ፣
4. ዝውውር ወይም ምድባ የተሰራለት ተሿሚ ደብዳቤው እንደደረሰው በመመሪያው በተገለፀው ጊዜ ውስጥ የስራ ቦታ ላይ ተገኝተው ሪፖርት ከአላደረጉ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፣
5. ወደ ሌላ ዞን የሚዛወሩትን ተሿሚዎች በወቅቱ ክሊራንስ መስጠትና ዞኑ አስፈላጊውን እንዲፈፅም ያስተላልፋል፣
6. ከምደባና ዝውውር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. ወደ ብሄረሰብ ዞኖች የሚደረግ ዝውውር

1. ከኦሮሚያ ዞን ወደ ሌላ ዞን ፍ/ቤት ለመዛወር የኦሮሞኛ ቋንቋ የሚችል ተሿሚ ማግኘት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊቀመጥ የሚችል ቢሆንም ግዴታው ግን ከሁለት ዓመት በላይ የሚበልጥ አይሆንም፣
2. ሌሎች የብሔረሰብ ዞኖች ቋንቋ ለማሳደግ ሲባል ቅድሚያ ቋንቋውን ለሚችሉ የብሔረሰብ ተወላጆች በብሔረሰብ ዞናቸው ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ምደባ ሊደረግ ይችላል።

18. የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

1. በዝውውሩ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ቅሬታውን ዝውውሩ በተሰራ በ 10 (በአስር) የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ከዞን ዞን የተደረገ ዝውውር ከሆነ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ማቅረብ ይኖርበታል፣

2. ፕሬዚዳንቱ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

3. በውሳኔው ላይ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ለዞን ንኡስ ጉባኤ ወይም ከዞን ዞን የተደረገ ዝውውር ከሆነ ለክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በሶስት የስራ ቀን ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል። ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

19. ተጠያቂነት

1. በዝውውር ቅጹ ላይ መሞላት የሚገባቸውን መረጃዎች አዛብቶ ያቀረበ የዝውውር ጠያቂ ከውድድር ውጭ ይደረጋል። በዲስፒሊን የሚያስጠይቀው ከሆነም እንዲጠየቅ ይደረጋል፣

2. የዝውውሩን ቅፅ እንዲያረጋግጥ ኃላፊነት የተሰጠው ኃላፊ እና ባለሙያ ሆን ብሎ ዝውውሩን ለማዛበት በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ሰጥቶ የተገኘ እንደሆነ አግባብ በአለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፣

3. የዝውውር ፎርሙን ወቅቱን ጠብቆ አለማሰራጨት እና አስሞልቶ ወቅቱን ጠብቆ አለመላክ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ሲሆን፤ የወረዳ ዳኛ ዝውውር ፎርምን የወረዳ ሰብሳቢ ዳኛ፤ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ዝውውር ፎርምን ደግሞ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፊርሞ በመሸኛ መላክ ይኖርበታል።

20. የዝውውር መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የዞን ዳኞች አስተዳደር ንዑስ ጉባዔ ከዚህ መመሪያ ጋር ባልተቃረነ ሁኔታ በሥሩ ያሉ ወረዳ ፍ/ቤቶች እና ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤቶች የዳኞችን እና የተሿሚዎችን ዝውውር ለመወሰን የሚያስችል የዝውውር መመሪያን ማውጣት ይችላል፣

2. የዞኑ የዳኞች አስተዳደር ንኡስ ጉባዔ የሚያወጣው የዝውውር መመሪያ በተቻለ መጠን የዞኑን ልዩ ሁኔታ እና የስራውን ፍሰት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የኔነህ ስመኝ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኞች አስተዳድር ጉባኤ ሰብሳቢ

በአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሥር በሚገኙ ፍርድ ቤቶች

ከአንድ የዞን ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ለሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ የተሿሚዎች የዝውውር መጠየቂያ ቅጽ-

01

1. የተሿሚው ስም ከአነያቱ_____ ዖታ_____ ዕድሜ__
2. አሁን የሚሰራበት ዞን _____ ወረዳ_____
3. በፍ/ቤት የአገልግሎት ጊዜ
   - 3.1 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.2 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.3 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.4 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.5 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
4. በሌላ መ/ቤት የአገልገሎት ጊዜ
   - 4.1 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.2 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.3 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.4 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.5 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
5. ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን_____
6. ለመዛወር የሚፈልጉባቸው ቦታዎች
   - 6.1 ዞን 1----------ወረዳ 1---------- 2---------- 3----------

6.2 ዞን 2----------ወረዳ 1---------- 2----------
3----------

6.3 ዞን 3----------ወረዳ 1---------- 2----------
3----------

7. ለመዛወር የሚፈልጉበት ምክንያት

7.1 በአገልግሎት ----------

7.2 በጋብቻ----------

7.3 በሕመም----------

7.4 በሌላ ምክንያት ከሆነ ይኸው ይገለጽ

---

10. እኔ ስሜና ፊርማዬ ከዚህ በታች የተገለፀው ዳኛ/ ተሿሚ ከዚህ በላይ ከዘረዘርኳቸው ቦታዎች ውስጥ በአንዱ ተዛውሬ እንድሰራ ስል አመለክታለሁ።

አመልካች_____

ፊርማ_____

ቀን_____ ቅፁን የሞላው ባለሙያ

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

ቀን----------

ቅፁ በትክክል ስለመሞላቱ ያረጋገጠው ሀላፊ

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

ቀን----------

ማሳሰቢያ፡- መረጃውን በትክክል አለመሙላት የዝውውር ጥያቄውን ውድቅ ከማድረጉም በላይ በህግ ያስጠይቃል።

ከአንድ ዞን ወረዳ ወደ ሌላ ዞን ወረዳ ዝውውር የሚካሄደው በዞኑ አማካኝነት ስለሆነ የወረዳው የዝውውር ቦታ በክልል ጠ/ፍ/ቤት እንደማይወሰን በቅድሚያ እንዲታወቅ።

በአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሥር በሚገኙ ፍርድ ቤቶች

ከአንድ የዞን ወደ ሌላ የዞን ወረዳ ለሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ የተሿሚዎች የዝውውር መጠየቂያ ቅጽ-02

1. የተሿሚው ስም ከእነአያት_____ ፆታ_____ ዕድሜ__
2. አሁን የሚሰራበት ዞን _____ ወረዳ_____
3. በፍ/ቤት የአገልግሎት ጊዜ
   - 3.1 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.2 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.3 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.4 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.5 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
4. በሌላ መ/ቤት ያገለገሉበት ጊዜ
   - 4.1 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.2 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.3 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.4 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.5 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____

5. ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን_____

6. ለመዛወር የሚፈልጉባቸው ቦታዎች

1 ኛ ከ----------ከ/ፍ/ቤት----------ወረዳ ወደ----------ከ/ፍ/ቤት----------ወረዳ

2 ኛ ከ----------ከ/ፍ/ቤት----------ወረዳ ወደ----------ከ/ፍ/ቤት----------ወረዳ

3 ኛ ከ----------ከ/ፍ/ቤት----------ወረዳ ወደ----------ከ/ፍ/ቤት----------ወረዳ

7. ለመዛወር የሚፈልጉበት ምክንያት

7.1 በአገልግሎት ----------

7.2 በጋብቻ----------

7.3 በሕመም----------

7.4 በሌላ ምክንያት ከሆነ ይኸው ይገለጽ

---

10. እኔ ስሜና ፊርማዬ ከዚህ በታች የተገለፀው ዳኛ/ ተሿሚ ከዚህ በላይ ከዘረዘርኳቸው ቦታዎች ውስጥ በአንዱ ተዛውሬ እንድሰራ ስል አመለክታለሁ።

አመልካች_____

ፊርማ_____

ቀን_____ ቅፁን የሞላው ባለሙያ

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

ቀን----------

ቅፁ በትክክል ስለመሞላቱ ያረጋገጠው ሀላፊ

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

ቀን----------

ቀን----------

ማሳሰቢያ፡- መረጃውን በትክክል አለመሙላት የዝውውር ጥያቄውን ውድቅ ከማድረጉም በላይ በህግ ያስጠይቃል።

ከአንድ ዞን ወረዳ ወደ ሌላ ዞን ወረዳ ዝውውር የሚካሄደው በዞኑ አማካኝነት ስለሆነ የወረዳው የዝውውር ቦታ በክልል ጠ/ፍ/ቤት እንደማይወሰን በቅድሚያ እንዲታወቅ።

በአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሥር በሚገኙ ፍርድ ቤቶች

ከአንድ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ የተሟሚዎች

የዝውውር መጠየቂያ ቅጽ-03

1. የተሟሚው ስም ከእነአያቱ_____ ዖታ_____ ዕድሜ__
2. አሁን የሚሰራበት ዞን _____ ወረዳ_____
3. በፍ/ቤት የአገልግሎት ጊዜ
   - 3.1 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.2 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.3 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.4 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
   - 3.5 በ_____ፍ/ቤት ከ----------ከ-------እና የቦታው ምድብ----------
4. በሌላ መ/ቤት ያገለገሉበት ጊዜ
   - 4.1 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.2 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____
   - 4.3 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____

4.4 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____

4.5 በ_____መ/ቤት ከ_____እስከ_____

5. ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን_____

6. ለመዛወር የሚፈልጉባቸው ቦታዎች

1 ኛ ከ----------ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ----------ከፍተኛ ፍ/ቤት

2 ኛ ከ----------ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ----------ከፍተኛ ፍ/ቤት

3 ኛከ----------ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ----------ከፍተኛ ፍ/ቤት

7. ለመዛወር የሚፈልጉበት ምክንያት

7.1 በአገልግሎት ----------

7.2 በጋብቻ----------

7.3 በሕመም----------

7.5 በሌላ ምክንያት ከሆነ ይኸው ይገለጽ

---

10. እኔ ስምና ፊርማዬ ከዚህ በታች የተገለፀው ዳኛ/ ተሿሚ ከዚህ በላይ ከዘረዘርኳቸው ቦታዎች ውስጥ በአንዱ ተዛውሬ እንድሰራ ስል አመለክታለሁ።

አመልካች_____

ፊርማ_____

ቀን_____ ቅፁን የሞላው ባለሙያ

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

ቀን----------

ቅፁ በትክክል ስለመሞላቱ ያረጋገጠው ሀላፊ

ስም----------

ኃላፊነት----------

ፊርማ----------

ቀን----------

ቀን----------

ማሳሰቢያ፡- መረጃውን በትክክል አለመሙላት የዝውውር ጥያቄውን ውድቅ ከማድረጉም በላይ በህግ ያስጠይቃል።

ከአንድ ዞን ወረዳ ወደ ሌላ ዞን ወረዳ ዝውውር የሚካሄደው በዞኑ አማካኝነት ስለሆነ የወረዳው የዝውውር ቦታ በክልል ጠ/ፍ/ቤት እንደማይወሰን በቅድሚያ እንዲታወቅ።